# <u>ግዙፍ መንግስት ጉርድ ዜጋ</u>

ከደቂቀ ኢዴፓ

በቅርብ የማውቀው አንድ ነጋዴ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ስልክ ይደውልልኛል፡፡ የመደናገጥና የመረበሽ ስሜት እንዳለው ድምጹ ያስታውቃል፡፡

" ከንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ አሁን ስልክ ደውለውልኝ ንግድ ፈቃድህን ባታድስ ሱቅህን አናሽጋለን፡፡ ሱቅህ ከታሸገ ድግሞ ለአንድ ዓመት ንግድ ፈቃድ ማውጣት እንደማትችል አታውቅም? አሉኝ ፡፡"

"አሁን ማለት በስንት ሰዓት ነው? የመጀመርያ ጥያቄዬ ነበር ?

"ሁለት ሰዓት ላይ! "

"እርግጠኛ ነህ ሁለት ሰዓት ላይ ነው ከጠቀስከው ቢሮ የተደወለልህ ?"

"አዎ፡፡ ያሉኝን እየነገርኩህ !"

ትንሽ ግር የሚል ነገር ነው፡፡ ከስራ ሰዓት ውጭ ያውም ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ግለስብ ስልክ ላይ ደውሎ ሰርቶ የመኖር መብትህን እስከአንድ አመት ድረስ አግድሃለሁ የሚልና ሕገ-መንግስታዊ መብትን የሚያሳጣ መርዶ መንገር ምን ዓይነት አስተሳሰብ የወለደው ድርጊት ነው? መልስ አልነበረኝም፡፡ አንድ ጥያቄ ግን ነበረኝ፤

"ለአንድ ዓመት ቤተሰብህንና እራስህን ምን እንደምትቀልብ መመርያ አብረው አልሰጡህም ?"

" እየቀለድክ ነው መሰለኝ !" አለ

ቀልዴን እንኳን አልነበረም፡፡ ጉዳዩ የሚታየው የግለሰብ መብት በተረጋገጠበትና ሶሻል ሴኩሪቲ ባለበት ሀገር ቢሆን ኖሮ በራሱ አቅም የስራ እድልን የፈጠረ ዜጋን ማፈናቀል ይቅርና መስራት የሰለቸው ዜጋም ቢሆን የመኖር ህልውናውን ማረጋገጥ የመንግስት ግዴታ ይሆን ነበር፡፡ መንግሰት ተጠያቂነትን ባይፈራ እንኳን ስራ የሌላቸውን ዜጎች የማኖር ኃላፊነት ስላለበት ለአንድ ዓመት ዜጋውን ከመስራት ሕገ-መንግስታዊ መብቱ ከማገዱ በፊት ደጋግሞ ማሰብ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በመነሳት በእርግጠኝነት መናገር የሚቻል ነገር ቢኖር ቢያንስ በአስተዳደራዊ ምክንያት ዜጎች ለአንድ ዓመት ያህል ያለስራ ተቀመጡ ወይም ለአንድ ዓመት ዞር ዞር ብላችሁ ተመለሱ እንደማይባሉ ብቻ ነው፡፡ ሰርቼ እራሴን ላስተዳደር የሚል ዜጋ የአርባ ቀን እድሉ አዞበት ካልሆነ በስተቀር መርጦኛል በሚለው መንግስት ለአንድ ዓመት ያህል ስራ አትስራ መባሉ ህለናውን የሚፈታተነው ጥያቄ እንደሚሆን ግልጽ ነው፡፡ መንግስታት ከልክ በላይ ሲጠናከሩና ስልጣናቸው ሲገዝፍ ግለሰቦችን ጉርድ አድርገው ማየታቸው የተለመደ እውነታ ነው፡፡

የነጋዴው ጓደኛዬ ጉድ ሲገርመኝ አመሸ፡፡ የሚዘጉ የንግድ ቤቶች ቁጥር እንዲጨምር ማድረግ ወይም በተለመደው ቋንቋ መቆጣጠር ያስፈለገው መጠነ ሰፊ በሆነ መልኩ የሚካሄደውን ነጋዴውን የመመዝገብና ከግምት በማይሻል ጥናት ግብር የመጣል ዘመቻ ስኬታማነትን ለማረጋገጥ ሲባል የግለሰቡ ውሳኔ ምንም ይሁን ምን ከስራ ሰዓት ውጭም ቢሆን ስራ አስፈጻሚዎች በግለሰብ ስልክ ላይ ደውለው ማስጨነቅና ማወከብ ነበረባቸው፡፡ አስፈጻሚዎችና ካድሬዎች ለኢኮኖሚው ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ አይጠበቅባቸውም፤ ደሞዛቸውም ወር ጠብቆ ይመጣል፡፡ የተረገጠ መብት ይረገጥ፣ የፈረሰ ይፍረስ ግዴታቸው ስታትስቲክስና ኮታ መሙላት ብቻ ነው!

ለማንም ሊገባ በሚችል ደረጃ ዜጎች ከግንዛቤ እጥረትም ሆነ፣ ከቸልተኝነት አሊያም ጊዜያዊ ጥቅም እያማለላቸው የወንጀለኛነት ባህሪይ የሌላቸውን ስህተቶች ሊፈጽሙ ይችላሉ፡፡ ይሄ ደግሞ ሰውኛ ባህሪይ ነው- ይህ ደግሞ ለመንግስትም ቢሆን አዲስ አይደለም፡፡ መንግስታትም የሰዎች ስብስብ ስለሆኑ ስህተት ደጋግመው ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ የተለመደም ነው፡፡ ምርጫ የሚያስፈልገውም ለዚህ ነው፡፡ ቁም ነገሩ ከውግዘትም ሆነ ከማሳደድ በፊት ሁለቱም ከስህተታቸው ለመማር እንዲሚችሉና እንደሚማሩ ግንዛቤ ከመውሰዱ ወይም እንዲወስዱ ከማገዙ ላይ ነው፡፡

እንደ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ባሉ ሶሻሊስት ዘመም መንግስታት ዘንድ የዜጎች ሉአላዊነት በራሱ ሙሉ ሆኖ በህገ-መንግሰት ውስጥ የመካተት እድል ቢያገኝም እንኳን የግለሰቦች ሁለንተናዊ የሙብት ጥያቄዎች የብዙ ነገሮች ተቀጥላ ናቸው፡፡ በደርግ ዘመን በሕገ-መንግሰት ደረጃ ውንግርግር ባለ መልኩም ቢሆን የግለሰብ ሙብት ቢሰፍርም ለህዝብ ጥቅም በሚል ድፍን መፈክርና በተለያዩ ደንቦችና መመሪያዎች ስም የግለሰቦችን መቀነት ከማስፈታት ጀምሮ ጥረው ግረው ያፈሩት ቋሚ ኃብት በጠራራ ጸሐይ መውረሱና በግል አቋማቸው ምክንያት በነጭ ሽብርም ሆነ በቀይ ሽብር ውስጥ መታቀፍ ባለመቻላቸው መሰደዳቸውና መገደላቸው የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ ለቡድን ሙብት ቆመናል በሚሉ ስርዓቶች ውስጥ ግለሰቦች ለብዙሃን ጥቅም በሚል መንገላታታቸው፤ ፈለጉም አልፈለጉም በርዕዮተዓለም ካልታቀፉ መገለልና መገፋት እጣ ፈንታቸው ነው፡፡

የዚህ ዓይነትና ተመሳሳይነት ያላቸው የግለሰብ የሙብት ጥሰቶች ማለቂያ እንደሌላቸው ብረዳም ለጽሑፌ በመነሻነት ስለሚረዳኝ የሌላ ጎረቤቴንና ወዳጄን ገጠመኝ ላክል፡፡

ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ ስልኩ ያቃጭላል፡፡ በዛ ሰዓት ብዙም ያልተለመደ ስለሆነ የተሳሳተ የስልክ ጥሪ ይሆናል በሚል የጥርጣሬ መንፈስ ስልኩን ያነሳል፡፡

ከመብራት ኃይል ነው የምንደውለው፡፡ ቁጥሩ … አይደለም?

“አዎ ነው ምን ልርዳችሁ ፡፡”

“አመልክተው ነበር ፡፡”

“አዎ አመልክቼ ነበር፡፡ ታድያ ያመለከትኩት እኮ ከጠዋቱ 3 ተኩል ላይ ነበር ፡፡”

“ሊሆን ይችላል፡፡ የኛ የስራ ሰዓት ከአንድ ሰዓት እስከ ምሽቱ አምስት ሰዓት ነው፡፡ የጥገና ሰራተኞቹን ይውጡና ይቀበሏቸው !”

እመቤት በዚህ ሰዓት አልችልም! አንደኛ ሰፈሩ የመንገድ መብራት የለውም፤ ሁለተኛ እየዘነበ ነው፤ ሦስተኛ ስልክ ደዋይ ማን እንደሆኑ አላውቅኩም! አራተኛ ጥገናው ስንት ሰዓት እንደሚፈጅ አይታወቅም፡፡ ቁጭ ብለን ማደር

ሊኖርብን ነው ማለት ነው? ቢያንስ ቀድማችሁ ብታስታወቁኝ ዝግጅት አደርግ ነበር ፡፡”

“ማሳወቁን ከሆነ አሁን አውቀዋል፡፡ የመብራት ኃይል ሰራተኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ከፈለጉ መታወቂያ ይጠይቁ፡፡ አሁን በደረሰዎት ተራ ካልተስተናገዱ መቼ እንደሚደርስዎት አይታወቅም፡፡ በዚህ ምክንያት ለሚፈጠረው ችግር ተጠያቂ የሚሆኑት እርሶ ነዎት፡፡” በማለት ስልኩ ጆሮው ላይ እንደተዘጋ አጫወተኝ ፡፡

“የጉድ ሀገር ገንፎ እያደር ይፋጃል” ይባላል፡፡ መቼስ ጤናማ አሰራር የዘረጋ ተቋም ከምሽቱ አምስት ሰዓት ላይ የግለሰብ ስልክ ላይ ደውሎ ተገልጋይን በርህን ከፍተህ ጠብቅ አሊያም የራስህ ጉዳይ ሊለው አይችልም፡፡ “ይህ ስህተት መሆን አለበት ወይም ወንጀል መስራት የፈለጉ ግለሰቦች ይሆናሉ፡፡ ለማንኛውም ሁኔታውን ጠዋት አጣራ አልኩት ፡፡”

ጠዋት የገጠመው “ብትፈልግ ተስተናገድ አለበለዚያ ተውው” አተካሮ ለዚህ መድረክ የሚመጥን ታሪክ ስላልሆነ እተወዋለሁ፡፡ ጎረቤቴ እስካሁንም ድረስ መስመሩ ችግር ያለበት በመሆኑ ምክንያት ለአደጋ መቼ እንደሚጋለጥ አያውቅም፡፡ የመብራት አገልግሎት የሚያገኘውም በስጋት ውስጥ ሆኖ ነው፡፡የፖሊስ፣ የመከላከያና የደህንነት ተቋማት የሚያደርሱት የሰብአዊ ሙብት ረገጣው ጉዳይ ሳይዳሰስ ብቸኛ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑት መብራት ኃይልና መሰል መንግስታዊ ተቋማት በአስፈጻሚዎቻቸው አማካኝት በግለሰብ ላይ የሚያደርሱት ኢኮኖሚያዊ ሙብት ረገጣን ለማስቆም አቤት የሚባልበት የለም፡፡ ቢኖርም እንኳ አጸፋውን ስለሚፈራ ተቋማቱ በዘፈቀደና ያለተቆጪ መስራት ከጀመሩ ዘመናት እንደተቆጠሩ የአደባባይ ሚስጥር ነው፡፡ ያለቅደመ ማስጠንቀቅያ መብራት በማጥፋታቸው በርካታ ፋብሪካዎች ከስረዋል፡፡ ለአደጋና ለጥገና የስልክ ጥሪ መልስ አለመስጠት የተለመደ ነው ፡፡ ያልተገባ ክፍያ ጠይቆ ካስከፈሉ በኃላ በይታሰብልሃል የግለሰብን ገንዘብ አለመመለስ ከግብር አስገቢው ጀምሮ ሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች የተካኑበት መገለጫቸው ነው፡፡ ያልተመጣጠነ ኤሌክትሪክ ከለቀቁ በኃላ ንብረት አውድሞ፤ በሰበብ አስባቡ የወደመ ንብረትን አለመተካት፤ በተራና በራሽን የሚሰጡ የመብራትና የውኃ አገልግሎት ለተከታታይ ቀናት በማቋረጥ የዘፈቀደ ምክንያት ማቀረብ፤ ሕግን ካወጡ በኋላ ሕግን ወደኋላና ወደፊት እያፈራረቁና እያሽጋገሩ ገንዘብ ለመሰብሰብ አገልግሎትን ለማቋረጥ መጠቀምና ወዘተ… በዓይነተኝነት የሚጠቀሱ ድርጊቶቻቸው ናቸው፡፡

ግለሰቦች የመብራትም ሆነ ሌሎች አገልግሎቶችን የሚያገኙት በምጽዋት ሳይሆን ገንዘብ እየከፈሉ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ውጣ ውረድ በገንዘባቸው ለሚገዙት አገልግሎት ለምን ይዳረጋሉ? መልሱ ከላይ የቀረበው ነው መንግስታት ከልክ በላይ ሲጠናከሩና ስልጣናቸው ሲገዝፍ ግለሰቦችን ጉርድ አድርገው ማየታቸው የተለመደ መሆኑ፡፡ የግለሰብ ጥያቄ የሚያጠነጥነው በአንድ በኩል በሚከፍለው ልክ በስርዓትና በአግባቡ የመስተናገድ መብትን ማረጋገጥና በሌላ በኩል ከኛ ውጭ አማራጭ የለህምና የት ትደርሳለህ የሚለውን ግልጽ የመብት ረገጣን ማስተናገድ ላይ ነው፡፡

ከላይ በምሳሌነት የቀረቡት ግለሰብ ከምሽቱ አምስት ሰዓት በዝናብና በጨለማ በቤተሰባቸውንና ንብረታቸው ላይ አደጋ ሊደቅን የሚችል አስጊ ሁኔታ ቢኖርም ሌላ አማራጭ አገልግሎት ሰጭ በሃገሪቱ እንዳይኖር ስለተደረገ አገልግሎቱን ለማግኘት ሲሉ ያለ ህግ አግባብ ያለመደፈር መብታቸውን ማስረገጥ ወይም አሳልፎ መስጠት ነበረባቸው፡፡ ነጋዴውም ሆነ ሌሎችም በርካታ ግለሰቦች የሚጠብቃቸው ፈተና ይህው ነው፡፡ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ብቸኛ ባለቤት፣ ሰጭና ከልካይ መንግስት ሲሆን መዘዙ ዜጎች የአስፈጻሚዎች የመብት ረገጣ ሰለባ መሆን ነው፡፡ የመብራት ኃይል፣ የቴሌ፣ የውኃና የሌሎቹም ብቸኛ መሰረታዊ አገልግሎት ሰጭ መንግስታዊ ድርጅት ስራ አስፈጻሚዎች የተሻለ የስራ እቅድና ፕሮግራም ከማውጣት ይልቅ የተገልጋይ ግለሰብን መብት በሚጥስና ለአደጋ በሚጋልጥ ሁኔታ ስራቸውን ለማስፈጸም ጉልበት የሚያገኙት ከላይ እንደጠቀስኩት ያለባቸው ተቀናቃኝ ባለመኖሩ የተጣለባቸው የአቅምና የችሎታ ማነስ እንደተጠበቀ ሆኖ "አማራጭ የሌለው ግለሰብ" የት ይደርሳል የሚል እምነት በውስጣቸው የተተከለ በመሆኑ ጭምር ነው፡፡

በርካታ መንግሰታዊ ድርጅቶችና ተቋማት እራሳቸውን ከሚያገለግሉት ህዝብ በላይ በማድረግ ያለበቂ ጥናትና ማስረጃ ወይም ለቁጥጥርና ለክትትል የሚያግዝ የአሰራረር ስርዓት ሳይዘረጉ ወይም ሕግ ፊት ሳይቀርቡ በግምት ላይ ተመስርተው ዜጎችን በጅምላ ግብር ባለመክፈል፣ ግብርን በማዛባትና ገቢን በመደበቅ ወይም ለመንግስት ባለመታመን ለመጠርጠርም ሆነ ለማሰር፣ ለማፈናቀል፣ ለመቅጣት የሚያስችላቸውን ውስብስብ ስልጣን ሲቀዳጁ ማየት እጅግ አሳሳቢ ነው፡፡ የመብት ጥሰቱም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለና እየታረመ ከመምጣት ይልቅ እየተባባሰ መሔዱ በተለይ ደግሞ የመብት ጥሰቱን ለማስፈጸም የሚተጉትን በምርጥና በታማኝ ዜጋነት በመውሰድ ቁጥራቸውን ለማብዛት ተተግቶ መሰራቱ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የግለሰቦችን መብት የሚጥሱትን አስፈጻሚዎች ለመሸከም እድል የሚሰጥ አስተሳሰብን በውስጡ ያረገዘ ሊሆን እንደሚችል ጠቋሚ ነው፡፡

ጸረ-ዴሞክራሲና ጸረ-ግለሰብ መብት የሆኑ ልማታዊ መንግሰታት (Developmental States) ግዙፍ መሆን የሚያስፈልጋቸው የግለሰቦች ፓለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ በማድቀቅ በቁጥጥር ስር ለማዋልና ግለሰባዊ እምነቱን በቡድን እምነት ውስጥ በማስገባት ለመበረዝና ለመከለስ ነው፡፡ በዚህ ደረጃ ግለሰቦችን ጉርድ ለማድረግ የሚቻለው መንግስት ጡንቻውን በማፈርጠምና ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ እራሱን ግዙፍ በማድረግ ብቻ ነው፡፡ ለተግባራዊነቱም ከሚቆጣጠራቸው እንደ ፖሊስ፣ መከላከያና ደህንነት ያሉ ዓይነተኛ ተቋማት በተጨማሪ ኢኮኖሚውን መቆጣጠር ወሳኝነት አለው፡፡ ስለዚህም መሰረታዊ አገልግሎትን የሚሰጡ በዜጎች ህልወና ላይ ወሳኝነት ያላቸውን ድርጅቶችና ተቋማት በግለሰብ እውቀትና የገንዘብ አቅም መገንባት ቢችሉም እንኳን እድሉን ለህዝብ ጥቅም በሚል መፈክር ስም በመቆጣጠር እራሱን ብቸኛው ባለቤት ማድረግ የግድ ይለዋል፡፡

አብዮታዊ ዴሞክራሲና ልማታዊ መንግስት(Developmental State) ተጣብቀዋል፡፡ መሰረታዊ አገልግሎትን በብቸኝነት ለመቆጣጠር ርዕዮተዓለማቸው ይፈቅዳል፡፡ አማራጭ በሌለበትም ይህንን "ካላሟላህ" ለአንድ ዓመት አትነግድም፤ ሰርተህ አትበላም ወይም የመብራት፤የውሃ፣ የስልክ፣የጤናና ሌሎች አገልግሎቶችን አታገኝም የሚሉ አስፈጻሚዎችና ተቋማት ድርጅቶችን መሸከምም ግድ ይሆናል፡፡ ይህኔ ግለሰብ ጉርድ ይሆናል፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የዜግነት ዓይነተኛ መገለጫ የሆኑት እንደ ሰርቶ የመኖርና ከህግ ውጭ ነጻነታቸው ያለመደፈር መብቶች በሕገ መንግስቱ ውስጥ በራሳቸው ሙሉና ፍጹም ሆነው ይገኛሉ፡፡ በዚህም ምክንያት እጅግ ለአዕምሮ የሚከብድ ወንጀል የሰራ ሰው እንኳን ፍርዱን ከጨረሰ በኃላ ሰርቶ ከመብላት በመለስ ያሉ አንዳንድ መብቶቹን ያጣ ይሆናል እንጂ ሰርቶ የመኖር መብቱ ገደብ አይጣልበትም፡፡ ለግለሰብ መሰረታዊ የሆኑ የመስራትና ያለሕግ ጥያቄ ያለመደፈር መብቶች ለቡድን መብትና ጥቅም ሲባል በጅምላና በዘፈቀደ በአስፈጻሚዎች መሸርሸርና መደፈር ሲጀምሩና አቤት የሚባልበት እድል በወረቀት ላይ ብቻ ሲቀር ሌሎች የግለሰብ መብቶችም ስር ከማጣታቸውም በላይ የአስፈጻሚ መጫወቻ ከመሆን አይድኑም ፡፡ የግለሰብ መብት ስር ካጣ ደግሞ የግለሰብ ስብስብ የሆኑት ቡድኖችም ሆኑ የብሔር ብሔረሰብ መብቶች ሊረጋገጡ አይችሉም፡፡

ዜጎች በተሟላ መልኩ ግዴታቸውን የሚያውቁና መብታቸውን የሚያስከብሩ የሚሆኑት ከማንኛውም ዓይነት የሞግዚት አስተዳደርና እኔ አውቅልሃለሁ ከሚል ቁጥጥር ነጻ ሲሆኑ ብቻ ነው፡፡ ማንኛቸውም ተቋማት ብቸኛ ሰጭና ከልካይነትን በማስቀረት፣ ከሃገር ባለቤትነት ጀምሮ የዜጎችን ግለሰባዊ መብትና የስልጣን ባለቤትነት ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ለማረጋገጥ እንዲሁም ከኢኮኖሚያዊ መብትም አኳያ ሰፊ ኢኮኖሚያዊ ግብአትን በማንቀሳቀስ እድገትንና ልማትና ለማረጋገጥ፣ ተመጣጣኝ ለሆነ ክፍያ ተመጣጣኝ አገልግሎትን ለማግኘት፣ ውድድርን በማስፈን ጥራትን ምርታማነት ለማረጋጋጥ ከተፈለገ የመንግስት ሚና በመጀመርያ ደረጃ በህግ የተገደበ ሆኖ በንግድና በኢንቨስትመንት መሰማራት ቅድሚያ ለግለሰቦች የሚተው መሆን ይገባዋል፡፡

የመንግስት ሚና “Night Watch Man” ሊሆን ነው ወይ ከሚል ስጋት የሚመነጭ ጥያቄ መነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ መንግስት ሁነኛ ሚናው መሆን ያለበት የሀገርን ሉአላዊነት ማስከበር፣ ሰላምን ማስፈን፣ የግለሰብን ኢኮኖሚዊና ፖለቲካዊ መብቶችን የማይጋፉ ፓሊሲዎችን መቅረጽና የመሳሰሉትን ሲሆን በሌላ በኩል ሞኖፖሊን ከመከላከል አኳያ መሰረታዊ አገልግሎቶቹ ባልተስፋፉበት ሁኔታ ጣልቃ ገብቶ በማስፋፋት፣ ውድድር በሌለባቸው የስራ ዘርፎች ውስጥ ተወዳዳሪ ሆኖ እየቀረበ ዜጎች ተገቢውን አገልግሎትና ተመጣጣኝ ክፍያ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣ አቅርቦት እንዳይመናመን ጉድለቶችን ማሟላትና በጥቅሉ ተያያዢነት ያላቸውን ተግባራት ማከናወን ናቸው፡፡

የመንግሰት ሚና ከዚህ ገድብ ሲያልፍ ግን የኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ሞተር የሆኑ አገልግሎቶችን በመቆጣጠር ፓለቲካውን ወደ መቆጣጠር ማምራቱ አይቀሬ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ የሕግ አውጭው፣ የሕግ ተርጓሚውና ሕግ አስፈጻሚው ሚና ተለይቶ ባልታወቀበትና በቅጡ ባልተጠናከረበት ሁኔታ ዜጎች የመንግስት ምርኮኛ (subjects) ላለመሆናቸው ማረጋገጫ አይኖርም፡፡ በተለይ ደግሞ መንግሰት ሲገዝፍ ለቁጥጥርና ለክትትል ስለማያመች አባካኝና ለሙስና የተጋለጠ ሁሉንም መቆጣጠር የሚፈልግ አንዱንም በቅጡ ማከናወንና ማጠናቀቅ የሚሳነው ይሆናል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥም ዋጋ ከፋዮቹ ሁል ጊዜም ዜጎች ናቸው፡፡

ይህንን ማነቆ በመስበር ዜጎች በሀገራቸው ሁለንተናዊ ጉዳይ ላይ ወሳኝ ሚና እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚቻለው ከህልውናቸው ጋር የተሳሰሩና መሰረታዊ አገልግሉትን የሚሰጡ ተቋማትን ከመንግስት ብቸኛ ቀጥጥር አውጥቶ ግለሰቦች በግል ወይም በጋራ ኃብትነት የሚይዟቸው የሚያለሟቸው መብቶቻቸው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን መንግስት አቅመ ደካማና ከሲታ ይሁን ማለት አይደለም፡፡ መንግሰት ለቁመናው የሚመጥን ልኬት ሊኖረው ይገባል፡፡ ቅልጥፍና እንዲኖረው ከተዘናጋበት በቀላሉ ተነስቶ ስራውን የሚያቀላጥፍ፤ ለመስራት ሲውተረተር የግለሰቦችን መብት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የማይጨፈልቅ ሸንቃጣ መሆን አለበት፡፡ ለዚህ አስተምህሮት አብዮታዊ ዴሞክራሲ እንደተለመደው የግለሰቦች ሰርቶ የመብላትና ከሕግ አግባብ ውጭ ያለመደፈር ጥያቄ በቡድኖች ወይም ብሔር ብሔረሰቦች ጥያቄ ውስጥ የታቀፈ ስለሆነ የብሔር ብሔረሰቦች ችግር ሲፈታ አብሮ ይፈታል የሚል እምነትን እያራመደ ይገኛል፡፡ እንደዚህ አይነቱን የመብት ጥያቄ ማስፈንም ሆን ማረጋገጥ የሚችለው መንግሰት ብቻ ስለሆነ የጋራ ሃብትን የማልማትና የማዳረስ ስልጣን በብቸኝነት በመንግሰት መያዝ እንዳለበት ስለሚታመን በመሰረታዊ አገልግሎትና በሀገራዊ ሃብት ልማት ላይ የግሰብን ተሳትፎ ይገድባል እስከነአካቴውም ይሸራል፡፡

በግለሰብ መብት ወስጥ ብቻ የሚገኝና በተናጠል ሊቀርቡ ከሚችሉ መብቶች መካከል ሰርቶ የመኖርና ያለ ሕግ አግባብ ሰብአዊ መብቱ የአለመደፈር ጥያቄዎች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በብሔር ውክልና ማዕቀፍ ውስጥ በጅምላ መቅረብ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም የሚገኘው መልስ የእንዳንዱን ግለሰቡ አቅምና ችሎታ ወይም የንግድና የኢንቨስትመንት ፍላጎት ግምት ውስጥ የሚየስገባ በመሆኑ ነው፡፡ ግለስብ መነገድ ወይም ኢንቨስት ማድረግ ሲፈልግ እንዴትና የትና ምን ልነግድ? መዋዕለ ንዋይስ ከየት ላግኝ? ይላል እንጂ የማን ብሔር አባል ነኝ? በየትኛው የብሔር ውክልና ልነግድ ወይም ኢንቨስት ላድርግ አይልም፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የግለሰብ ሰርቶ የመኖርም ሆነ ከሕግ ውጭ የመደፈርና የህግ ከለላ የማግኘት የመብት ጥያቄ የሚመለከተው በቡድን መነጽር ውስጥ ስለሆነ ቅድሚያ ከሚሰጠው የቡድን መብት በኃላ ተራ ጠባቂ አድርጎታል፡፡ ርዕዮተ ዓለሙም በግለሰቦች ላይ እምነት ስለሌለውና የግለሰቦችን ሁለንታናዊ የመብት ጥያቄን የቡድንና የብሔር ብሔረሰቦችን የመብት ጥያቄ እንደሚተረትር አድርጉ በጥርጣሬ ዓይን ስለሚመለከተው ይህንን ለመከላከል ሲባል መሰረታዊ የሆኑ ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን በመቆጣጠር እራሱን ግዙፍ፤ ግለሰብን ጉርድ ማደረግ ብቸኛው አማራጭ አድርጎ ይወስዳል፡፡ ስርዓቱም ሆነ የስርዓቱ አስፈጻሚዎች ኮታቸውንና ስታትስቲክሳቸውን ለማሟላት የግለሰብን የመኖር ህልውና ለመፈታተን የሚደፍሩትም ሆነ ከሕግ ውጭም ቢሆን መብትን ጥሰው ከተጠያቂነት የሚድኑት ቅድሚያ የቡድንና የብሔር ብሔረሰቦችን መብት ከማረጋገጥ አኳያ የግለሰቡን መብት መጨፍለቅ ሕገ-መንግስታዊ ጥሰት መሆኑን የመረዳት ውዠምብርም ስላለባቸው ነው ፡፡

ለዚህም በርካታ ምሳሌዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ በዋነኛነት በህዝብ ሃብትነትና በግለሰብ ግብር ከፋዩች መዋጮ የተቋቋሙት መገናኛ ብዙኃንን እንመልከት፡፡ የመገናኛ ብዙኃን ዜጎችን እኩል ማገልገል ህገ-መንግስታዊ ግዴታቸው እንዳለባቸው ለአፍታም ሊረሱ አይገባም፡፡ የኢትዮጵያ ቴሌቭዥንና ሬድዮ ግን የብሔር ብሔረሰቦችን ህገ-መንግስታዊ መብት የሚነኩ ጉዳዮችን እንጂ የግለሰብ ህገ-መንግስታዊ መብትን የሚነኩ ጉዳዮችን ማስተላለፍም ሕገ-መንግሰታዊ መብትን እንደመጋፋት አይቆጠሩትም፡፡ እነኚሁ የመገናኛ ብዙኃን ቀንና ማታ የንግድ ፈቃድ ምዝገባ ያላሟላችሁ ግለሰቦች ወደፊት ንግድ ፈቃድ ለማውጣት አትችሉም እያሉ ሲያሳውጁ የግለሰብ ሰርቶ የመኖር መብት የሚጻረር ድርጊት መፈጸማቸውን ከግምት ውስጥ አያስገቡም፡፡

ለታላቁ የምዕተ-ዓመቱ የአባይ ግድብ ቦንድ ያልገዛና ገንዘብ ለማዋጣት ፈቃደኛ ያልሆነን ግለሰብ “ኢትጵያዊነቱ እንደሚሻር” የሚለፍፉ ዛቻዎችንና አስተያየቶችን ሲያስተላልፉ የዜጎችን የመቃወምና ያለፈቃዳቸው ያለመተባበር የዜግነት መብታቸውን መንጠቃቸውን አያስተውሉም ወይም የግለሰብ ጉዳይ ስለሆነ ግድ የላቸወም፡፡

ይህንን ሲፈጽሙ ሕገ-መንግስቱንም ጨምሮ ማንኛውም ምድራዊ ሃይል ያልተሰጠውን ዜግነትን የማደላደል አደገኛ ተግባርን እያበረታቱ መሆኑን የተገነዘቡት አይመስለኝም፡፡ የታላቁ የአባይ ግድብ ግንባታ በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረው ሁለንተናዊ ጥቅም አሌ ሊባል አይችልም፡፡ ይህንን ጥቅም ለማረጋገጥ የተለያዩ የህዝብ ግንኙነት ስራ በመስራት የዜጎችን ሁለገብ ተሳትፎ ማጎልበት አግባብ ነው፤ ያላወቁ ማወቅ አለባቸው እውቀት ቀና ልቦናን የመተባባር መናፈስን ይወልዳል፡፡ ከዚህ ውጭ ግን የግድቡ አስፈላጊነት የቡድንን መብት ከማረጋገጥ አኳያ ብቻ ተቃኝቶ፣ ከግድቡ በፊት የተፈጠረውን የግለሰቦች የመጠየቅ፣ የመጠራጠርም ሆነ ያለመተባበር መብታቸውን አሳልፈው እንዲሰጡ ለማድረግ ቅድመ ማሸማቀቅና ማሸበር መዘዙ ብዙ ነው፡፡ ቅድመ ኢህአዴግ በነበረው የደርግ ስርዓት "ለወዛደሩ አምባገነንነት" በሚል መፈክር ጥላ ስር እንደዋዛ የተጀመሩ የአትናገርና የአታስብ መግለጫዎች የኃላ ኃላ ሱስ እየሆኑ ሄደው "የፍየል ወጠጤን" ለማቅራራት በር እንደከፈቱ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ዜጎች ግብር መክፈል አለባቸው፡፡ ይንንም መብታቸውን በፈቃዳቸው ለመንግሰት አሳልፈው የሰጡት የውዴታ ግዴታቸው ነው፡፡ በእምነት ደረጃ እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ዜጎች ግብር የሚከፍሉት መንግስትን ከራሳቸው በላይ ስለሚያዩ ወይም ደሞዝ እየከፈሉ እንዲያስተዳድሩቸው ያቋቋሟቸው መንግስታዊ ተቋማት ብቃትቸውን ማረጋገጥ እየተሳናቸውና በቸልተኝነትነት አሊያም በማንአለብኝነት እንዲያተራምሷቸውና እንዲያወኳቸው ሲያሻቸውም መሰረታዊ መብቶቻቸውን እንዲጨፈልቁ አይደለም፣ በታሪክም ውስጥ እንዲህ አልተጻፈም፡፡ ይልቁንም ዜጎች ከግለሰባዊ መብታቸው ቆንጥረው ለመንግስታትና ለመንግስታዊ ተቋማት መብታቸውን አሳልፈው የሚሰጡት አብሮነትን የሚጠይቁ የጋራ ጥቅሞቻቸው እንዲከበሩላቸውና እንዲያረጋግጡላቸው፣ አቅማቸውን ባመዛዘነና ህልውናቸውን በማይነካ መልኩ እየተለካ ግብር ከፍለው አገልግሎቶችንም በአግባቡ እንዲያገኙና ለመሳሰሉት ጥቅሞቻቸው ነው፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ግን እየሆነ የሚገኘው ይህ አይደለም፡፡ ዜጎች ግብር የሚከፍሉት መንግስትና መንግስታዊ ተቋማቱ የዜጎችን የጋራ ጥቅሞች ከማስከበርና ዜጎችም በመከባበርና በመቻቻል ሃገራዊ ሃብታቸወን በመጋራት እንዲጠቀሙ ይህንንም ለማስፈጸም እንዲረዳ አቅማቸውን ያመዛዘነና ህልውናቸውን የማይነካ ግብር መክፈላቸው ቀርቶ የመንግስትን መሻትና ፍላጎት ለማረጋገጥ አሊያም ታሪክን ለመስራት በሚደረግ እሽቅድድም የሚለካ ሆኖል፡፡

ግብር አስገቢ መንግስታዊ ተቋም ግብር ከፋዩን ዜጋ በጅምላ ከመጠርጠራቸው በፊት በመጀመርያ የአሰራረር ስርዓት በመዘርጋት በቁጥር፣ በጥናትና በመረጃ ላይ ተመስርቶ ጥፋተኞችን አንጥሮና ለይቶ ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡ የሆነው ግን የተገላቢጦሽ ነው፡፡ መስሪያ ቤቱ ከስልጣኑ ውጭ በመሄድ ከግምት ባልተናነሰ የስሚ ስሚ ጥናት ላይ ተመርኩዞ ዜጎችን ግብር ባለመክፈልና ገቢን በመደበቅ በጅምላ ጠርጥሯል፡፡ በግምት የተመነውንም ግብር ከላይ በገለጥኩት መንገድ ሕገ-መንግስታዊ መብትን ምርኮኛ አድርጎና ሙስናን በሚያበረታታ መልኩ አስፈጻሚዎች ከዜጎች ጋር እንዲደራደሩ አድርጓል፡፡ ዜጎችም አማራጭ ስላልነበራቸው የድርድሩ አካል እንዲሆኑ ተገደዋል፡፡

አዲሱን የግብር ተመን እንዲያጠኑና እንዲተምኑ የተመደቡት ተማሪዎች ግምቱን የሰሩት በአስር ወይም በአምስት ደቂቃ እይታ ነው፡፡ ንግድ ተለዋዋጭ ባህርይ ስላለው፤ ሁሌ ፋሲካ የለም፡፡ ገቢያ ይወጣል ይወርዳል፡፡ በዚህም ምክንያት እወነተኛ የገበያ አቅም ለማወቅ ለወራት እቦታው ላይ ተገኝቶ ጥናት ማድረግ ግድ ያላል፡፡ ከዚህም ወጣ ብለን ስንመለከተው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ነጋዴዎች አይደሉም፡፡ አጭር ስልጠናም የንግድ እውቀታቸውን በአንዴ አዳብሮት ግምታቸው ብቸኛው በውሳኔ ምንጭነት ሊያገለግል አይችልም፡፡ ያቀረቡት መረጃም ዜጎችን ለመጠርጠር መነሻ ሊሆን አይገባም፡፡

ከላይ እንዳየነው ግብር አስገቢው ቢሮም ሆነ ነጋዴዎች ገማቾች ናቸው፡፡ ልዩነቱ ነጋዴዎች ስልጡን ገማቾች ሲሆኑ ተማሪዎች ግን ተማሪ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያትም ንግድ ሚኒስቴር ካንተ ግምት የኔ ግምት ይበልጣል ለማለት ስልጣኑ መብት ካልሆነው በስተቀር ሕጋዊ መብቱ አጠያያቂም፣ አከራካሪም ነው፡፡

ዜጎች በእለት ተእለት ህይወታቸው ውስጥ ከግለሰብም ሆነ ከመንግስትና ከመንግስታዊ ተቋማት ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ላይ ፍትሕን ለማግኘት ተጨባጭ ማስረጃ ያስፈልጋቸዋል፡፡ መንግስትና መንግስታዊ ተቋማትም ቢሆኑ የተለየ መንገድ የላቸውም፡፡ ያለ ማስረጃ በጅምላ ዜጎችን መጠርጠር ከስልጣናቸው ከሚመነጭ አቅም ካልሆነ በስተቀር ከሕግ አኳያ ሚዛን የሚደፋ መነሻ ሊኖራቸው አይችልም፡፡

ከላይ በሰፊው ለማየት እንደሞከርኩት መንግስታት ብቸኛ አማራጭ በመሆን በሚፈጥሩት ጡንቻና ርዕዮተ ዓለም በግለሰቦች መብት በሚቸራቸው የበላይነት መንፈስ የዜጎች መብት በተቋማትና በአስፈጻሚዎች ሲጣስ ማወራረጃ መንገድ የለም፡፡ የግለሰብ ጉዳይ የግለሰብ ጉዳይ ነውና ቸል ያባላል አውቆ ይረሳል፡፡ የግለሰብ ጉዳይ ግን በሂደት የማህበረሰብ፣ የቡድን አልፎ ተርፎም የብሔር ብሔረሰብ ጉዳይ መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡

እስካሁን ያነሳነው እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት ውጤት የሆነውን ሌላ ገጽታ እንመልከት፡፡ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሳብ ውስጥ ከሰውም ሰው፣ ከዜጋም ዜጋ አለው የሚያሰኙ ድርጊቶችን መመልከት የተለመደ ነው፡፡ ለዚህ በመገለጫነት ሊነሳ የሚችለው መገናኛ ብዙሓን ሰሞኑን በስፋት ከተያዙት ጉዳዮች መካከል አንዱ የሆነውና በቁጥራቸው ጥቂት የሆኑ አርሶ አደሮችንና በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ውስጥ የተደራጁትን ሚሊየነር የማድረግ ስብከት ነው፡፡ ስብከቱም በሕገ-መንግስቱና በድንጋጌዎቹ ውስጥ የሰፈሩትን ዜጎችን እኩል የማየትና ያለማበላለጥ ግዴታዎችን የሚጻረር መሆኑን እንደተለመደው ግንዛቤ የተወሰደበት አይደለም፡፡

እጅግ ስር የሰደደ የኑሮ ድቀት በተንሰራፋባት ኢትዮጵያ በቁጥራቸው ጥቂት የሆኑ ዜጎችን ከግብር ነጻ በማድረግ ያለተወዳዳሪ ብቸኛ አቅራቢ እንደሆኑ በማመቻቸት ፣ መሬትና መስል ህዝባዊ ሀብቶችን በነጻና ያለውድድር በመስጠት "ሚሊየነር" ለማድረግ እየተሰራ ያለው ዘመቻ ኢ-ህገመንግስታዊ ነው ! በውስጡም ስውር በሆነ መንገድ ዜጎችን እኩል ያለማየት ችግር ያለበት ነው፡፡ ዘመቻው በተለይ ደግሞ በአነስተኛና ጥቃቅን ከተደራጀውና ከአርሶ አደሩም በላይ በመሄድ ከነጋዴውም መካከል ጥቂት ነጋዴ ቆንጥሮ ልዩ ጥበቃ እንዲያገኙ በማድረግና "እኛ የፈጠርነናቸው ሚሊየነሮችና የኢህአዴግ ደጋፊ ነጋዴዎች" እያሉ በማሞካሸትና አደራጅቶ ከቀሪው ነጋዴ በመነጠል ለስርዓቱ ታማኞችን የመፍጠር ጥረቱ ግልጽ የሆነ መድልዎ ከመሆኑም በላይ ዴሞክራሲውን ለሁሉም ዜጎች እኩል በማዳረስና በማረጋገጥ ትግል ላይ ተጨማሪ ሸምቀቆ የማጥበቅ ድርጊት ከመሆን አይዘልም፡፡ በየትኛውም መለኪያ የመንግስትን ሚና ጥቂት ታማኝ "ሚሊየነሮችን" በመፍጠር ስርዓቱን ከለውጥ መከላከል ሳይሆን በመካከለኛ ገቢ የሚተዳደሩ በርካታ ዜጎችን በመፍጠር በሰብአዊ መብት በኢኮኖሚያዊ መብቶች ላይ የተለየ ተጽእኖ ፈጣሪዎች እንዳይኖሩ ማድረግ ነው፡፡ የዴሞክራሲ ዋስትና የሚረጋገጠውም ያኔ ብቻ ነው፡፡

ከላይ ለማየት እንደተሞከረው ኢትዮጵያ ውስጥ የመንግስት ልዩ ጥበቃና ድጋፍ የምታገኘው በግለሰብነትህ ወይም በዜግነትህ አይደለም፡፡ አቅም ካለህ በአቅምህ ምክንያት በዴሞክራሲውና በኢኮኖሚው ላይ ልትፈጥረው የምትችለው ተጽእኖ ታስቦ ልዩ ትኩረት ታገኛለህ፡፡ በንግድ እንቀስቃሴህም ውስጥ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ታገኛለህ፡፡ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዙሪያ ለመጠለል ከፈቀድክ ምንም ዓይነት ካፒታል፣ እውቀትና ክህሎት ባይኖርህም በአነስተኛና ጥቃቅን ስር ትደራጃለህ፡፡ መሬትና ብድር ታገኛለህ፡፡ ልዩ ጥበቃ የሚደረግለት ገበያ ይመቻችልሃል፡፡ አንደ እስፈላጊነቱም ከግብርም ነጻ ልትሆን ትችላለህ፡፡ መገናኛ ብዙሃንም እንደዚህ ዓይነቱን ሃገራዊ ሃብትን እኩል የመጠቀም የዜጎችን ህገ-መንግስታዊ መብት የሚጻረር ድርጊት ከመንግስት አፍ ተቀብለው እንደ ድል በመቁጠር ያውጃሉ፡፡

በግብር ከፋዩ ህዘብ በሚሰበሰብ ሀገራዊ ሃብት ያለውድድር ልዩ ጥበቃ እያገኙ መነገድ የሚቻል ከሆነ በእውነቱ ሚሊየነር መሆንን ማንም አይጣላም፡፡ መንግስት ለሁሉም ዜጎች እኩል የመስራት እድል እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት ውጭ ሚሊየነር የመፍጠር ኃላፊነት ሲወስድ የታየው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር በሌላ ሃይል ተሞክሮ አያውቅም፡፡ የተለየ መደብን ጥቅም አስጠብቃለሁ የሚለው ሶሻሊዝምም እንኳን እያንዳንዱ እንደ ችሎታውና እያንዳንዱ እንደፍላጎነቱ ነበር መፈክሩ፡፡ ነፍሱን ይማረውና¡

ይህ ሁሉ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጥረት የግለሰቦቸን የመብት ጥያቄ ከቡድን አስተሳሰብ ውጭ ባዶ ለማድረግና ግለሰባዊነት ለማንበርከክ የሚደረግ ጥረት ውጤት ነው፡፡ የግለሰብ መብትንና የቡደን መብትን የማረጋገጥ የርዕዩተ ዓለም ትግሉ ባልከፋ ነበር ምክንያቱም የርዕዮተ ዓለም ትግሉ የዴሞክራሲ አይነተኛ መገለጫ በመሆኑ ነገር ግን ችግሩ የሚጀምረው ግለሰቦች በሀገራዊ ሃብት ላይ የመወሰን አቅማቸው ባልተገነባበትና መሬት፣ መዋዕለ ንዋይ፣ የስራ እድል ፈጠራ ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ በመንግሰት እጅ በተያዘበት ሁኔታና መንግሰት ብቸኛው ሰጭና ከልካይ አደራጅና አዋዋይ በመሆኑ ነው፡፡

በጥቅሉ ከላይ የቀረቡትን ገጠመኞች ስናጤናቸው የመንግስት ሚና በቅጡ ባልተገደበበትና ቁመናው ከግለሰቦች መብት በሚያከብርበት ሁኔታ ካልተከረከመ ሀገራዊ ሀብት ደህንነት፣ መከላያንና ፖሊስ ጨምሮ የመብራት ፣ የቴሌኮሙንኬሽንና የውኃ አቅርቦት በጥቅሉ መሰረታዊ የሚባሉት ኢኮኖሚያዊ ተቋማትን በሚቆጣጠርበት ሁኔታ የህዝቦችን የመወስን አቅምና ብቃት በማዛባትና በመቆጣጣር የህዝብ ይሁንታ የሚረጋገጥበትን የምርጫ ሂደትና ውጤቱን በቀጥታም ሆነ በእጅ አዙር መገልገያው ለማድረግ አለመቻሉን ማረጋገጫ ማግኘት አይቻልም፡፡ እመኑኝ ለህዘብ ጥቅም ነው የቆምኩት ብሎ መማልና መገዘትም መፍትሔ አይደለም፡፡ ምርጫ የሚያስፈልገውም መንግስታት ችግር ስለሚኖርባቸው ህዝቡ በፈቀደውና የተሻለ አስተሳሰብና አቅም ባለው ሃይል እንዲተኩ ወይም የህዝብን ይሁንታና መተማመኛ እንዲያገኙ ሲባል ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ብቸኛው መፍትኼ መንግስት እራሱን ታአምራዊ ሃይል ለማስመሰል እንደመሳርያ የሚጠቀምባቸው መሰረታዊ የሆኑ ኢኮኖሚዊ አውታሮች እንደአስፈላጊነቱ በጋራ ሃብትነት በሼር ወይም በተናጥል በግልም ሆነ በመንግስት እየለሙ ውድድር ጥራትና አቅርቦትን የሚስፋፉበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡ ይህ ደግሞ ሊረጋገጥ የሚችለው የመንግሰት ሚና ከዜጎች በላይ በተንሰራፋበትና በገዘፈበት ሃገራዊ ሃብትን በመቀራመትና ጥቂቶችን ሚሊዬነር በማድረግ የስርዓቱ ልዩ ተጠቃሚና ልዩ ጠባቂ ለሚፈጥረው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ውስጥ ሳይሆን የግለሰብ መብት በግሉም ሆነ በተደራጀ መልኩ ሲቀርብ ከምንም በላይ በሚከበርበት በሊብራል ዴሞክራሲ ውስጥ ብቻ ነው፡፡

ሊብራል ዴሞክራሲ ኃብትን ከብዙሃኑ ላይ ተቀራምቶ በማሰባሰብ የተለየ መደብን ሚሊየነር የማድረግ መንገድን አይከተልም፡፡ ሊብራል ዴሞክራሲ የዜጎችን ሃብት በመቀራመት ጥቂት ታማኝ ሚሊዬነሮችን ከመፍጠር ይልቅ፤ ሁሉም ዜጎች ሃገራቸው ባፈራችው ሃብት ላይ እኩል የመስራት፣ የመጠቀምና የመበልጸግ እድልን ያመቻቻል፡፡ ሂደቱ በሚፈጠረው ልማትና እድገትም አማካኝነት አብዛኛዎቹ ዜጎች እራሳቸውን የሚችሉ የትኛውም ኃይል ሆነ አሰተሳሰብ በኢኮኖሚያዊ ልዩ ጥቅምና ጥገኝነት መብትና ግዴታቸው ያልተቀየደ፤ ተመጣጣኝ የገቢ አቅም የገነቡ ዜጎችን በመፍጠር በፖለቲካዊም ሆነ በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የመወሰን ክህሎታቸውን ያዳበሩ፣ መብትና ግዴታቸውን የሚያሰከብሩ፣ ጥቅማቸውን አሳልፈው የማይሰጡና የማይወናበዱ ዜጎችን መፍጠር ነው ፡፡